## ወደ ሃገር ቤት

**ወደ ሃገር ቤት ወደ ልጅነት**
**እትብታችን ወደተቀበረበት**
**ጥርሳችንን ወደ ነቀልንበት**
**የኩበቱ ሽታ የሚናፍቅበት**
**ማንነት ሲለካ ሚዛን ሚደፋበት**
**ወደ እናት ጉያ  ወደ እናት ማጀት**
**የፍቅር ምድር የሰላም ገነት**
**ወደ ሃገር ቤት ወደ ሃገር ቤት**

A.D.T
Houston, TX
January27, 2010

## አመል

**አመል ስጠ ቢሆን ሽንብራን ተክቶ**
**ጸሀይ ብናሞቀው ከቤታችን ወቶ**
**ገለባ ማንነት እንክርዳድ የሞላው**
**ተቆልቶ ቢወገጥ መዐት የነበረው**
**እፍኝ አልሞላ አለ ዱቄት አምጣ ብለው**

A.D.T
Houston, TX
February 16, 2010

**ከጸጉሩ ወይስ ከጸጉሩ ሰር ካለው?**

**ደራሲ ከያኒ ጸሃፊ ሰአሊው**
**ወረቀት ከብእር አፋጭቶ ሊያሰፍረው**
**ብሩሹን ከሸራ አሻሽቶ ሊኩለው**
**ያረገዘውን ህልም ወልዶ እንዲስመው**
**የህይወትን ሰም ወርቅ አርጎ እንዲያቀርበው**
**ጭሮ እንዲበላ አንድ ቀን ሳይርበው**
**ችሎታው እንዲሆን መኖሪያ እንጀራው**
**ከጥበቡ ጅረት ምንጩ ከማያልቀው**
**ከሁሉ ተመርጦ ጥበብ ተለገሰው**

**መነሻ ጅምሩ ከሆነ ችሎታው**
**ቀኝ የዋለውን ህዝብ ግራ ባያጋባው**
**ጸጉሩን አሳድጎ ጉንጉን የጀበነው**
**ጠላልፎ ገምዶ ጅራፍ ያስመሰለው**
**የተጠበበት የአሃዱ መፍለቂያው**
**ከጸጉሩ ወይስ ከጸጉሩ ሰር ካለው**
**ከጭንቅላቱ ነው?**

A.D.T
Houston, TX
January 06, 2010

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot****. You may contact Amanuel Teweldeberhan  for comments at*** *amanuel1111@yahoo.com*